## ኃይማኖት!

አፍሪካ ደንቁሮ ኋላ እንዲቀር
የነሱን ኃይማኖት ሲያመልክ እንዲኖር
ክርስትያኑ ምስኪን ወደ ኢየሩሳሌም
እስላሙም ሓጂነት ሜካ እንዲያዘግም
ያዘዙበት ፍርጃ አልገባውም ገና
ዓይኑ በኃይማኖት ተሸፍኗልና!
ሁሉም የየራሱን "ኃይማኖቴ" ሲል
እስቲ ማን ነው ብልጡ፣ ማነው'ሳ ቂል!
የራሱን ሃብት ንዶ የባዕድ ሊክብ
ያገሩን ሃብት ወስዶ ከዚያ ሊያስረክብ...

የቱ ከሩቅ መጣ፣ የቱ ነው የቅርብ
ክርስትና ከአይሁድ፣ እስላም ከዓረብ
ለኛ ምናችን ነው፣ እነሱ ይጣሉበት
እስላም ከክርስትያን ሰላም እንኑርበት
ሁለት ወንድማሞች ሆድ-ጀርባ ሆነን!
በኃይማኖት ረገድ አለያይተውን
ሓበሻ ለሓበሻ ከፋፍለውናል
በባዕድ ሃይማኖት አጣልተውናል!
እስላም፣ ክርስትያኑ አብሮ ቢፋቀር
እስቲ አሁን ምን አለ በሰላም ቢኖር?

ይህ አልበቃ ብሎ እኛ ስንጣላ
ስንዋጋላቸው፣ እንዲህ ስንባላ
እነሱ ዳር ቁመው ሲያፌዙ፣ ሲስቁ
ውሃችን ሲጠጡ፣ ሃብታችን ሲዝቁ
ሲሰለጥኑና በልጽገው ሲልቁ
ክርስትያን እና እስላም ብለው ያለያዩን
ኋላ-ቀር ሆነን አቈልቍለው ሲያዩን!
"ጥቁር አህያ ነው" ብለው ሲያሰቃዩን
ጣምራ ጠላቶችን እንወቅ ለይተን
አዙረን ማየት ነው ዓይናችንን ከፍተን?

መጽፍሓና መስቀል ይዘው ስናያቸው
ቅዱሳን ሊመስሉ ረዝሞ ያ ጺማቸው
የኢትዮጵያ አምላክ፣ አድነኝ አቤቱ!
የልባቸው ተንኰል መጫኛ ርዝመቱ
ጃንጥላውን ተክለው፣ አንጥፈው ስጋጃ
ኃይማኖት ዘርግተው እንደ መጋረጃ
ዓይናችንን ጋርደው ያደነቈሩንን
ባዕድ መሆናቸውን ማየት አቃተን!

የጠነሰሱትን ተንኰል አናይም ወይ!
ለያይቶ፣ ከፋፍሎ፣ አጣልቶ መያዝ
ጦር ማንሳትም የለ፣ የጦር አበጋዝ

ራሱ ሲቆራረጥ መች ያሻል መጋዝ?
ይቅር ኤርትራዊ የትናንት ኢትዮጵያ
ከግብፅ፣ ከእስራኤል፣ ከዓረብ፣ ከሊብያ
መልኩም ይቀርበኛል ሱዳን፣ ሶማሊያ…

አምላክ እንደ ፈረስ ወይም እንደ በቅሎ
በኔ ስም ይጠራ፣ የኔ ነው ተብሎ
“የእስራኤል አምላክ” “የመሓመድ አምላክ”
ምን ጐድሏት አፍሪካ፣ እንዴት አምላክ የላት?
እንዴት አምላክ የላት፣ ኢትዮጵያ ምን ጐድሏት?
አረ እግዚኦ በሉ፣ ተው ይህን ዕብደት
አምላክ ፈጣሪ ነው፣ የለውም ባለቤት
ከሌሎቹ በፊት፣ ከጥንቱ ዘመናት
በችግሯ “አለሁ!” ብሎ የቆመላት
ለኢትዮጵያም እኮ አምላኳ አለላት!

ተው ወገኖቼ፣ ተው እንፋቀር
መለስ ብንል’ና ዘራችን ቢቈጠር
አንድ፣ ሁለት ብለን ሳይሞላ ስንዝር
የተረገዝንበት አንድ ሆድ ነበር…
ንጹሕ አፍሪካዊ፣ አዲስ ኃይማኖት
“የኢትዮጵያ አምላክ” ብለው የሚሉት
“አለሁ!” የሚል ጌታ አምነው ሲጠሩት
“የኢትዮጵያ አምላክ” ብቻ እመኑበት
ሌሎቹን ትታችሁ በእርሱ ተመኩበት።

እስላም፣ ክርስትያኑ ይቅር አትጣሉ
በዓረብ፣ በእስራኤል በቃ! አትታለሉ
በኢትዮጵያ አምላክ ብቻ ተማማሉ
እርሱን ብቻ ያዙ፣ ሌላን ወድያ በሉ!
የቀረውን ሁሉ አውጥታችሁ ጣሉ
የባዕድ ኃይማኖት ለኛ ምናችን
ወንድም ከወንድም ጋር የሚያጣላውን
ተነሱ እንገስግስ በቀናው ጐዳና
እንድትበለጽግ አገር ሰላም ሆና
ተበራቱ ጐበዝ፣ በሉ ቀና! ቀና!

ገ/ኢ. ጐርፉ።

**Back to Meskot**

---

***The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot*. ***You may contact G.E. Gorfu for comments at*** gegorfu@yahoo.com.